# *ወጣቱ ትዉልድ*
# *ዛሬም የኢትዮጵያ ሕዝብ ተስፋ ነዉ*

(በምሥራቅ አፍሪካ የኢሕአፓ ቅርጫፍ የተዘጋጀ )

ሀገራችን ኢትዮጵያ የገናና ታሪክ ባለቤት ለመሆን የበቃችዉ በአዛዉንት ዜጎቿ ብልህና የሰከነ አመራር ብቻ ሳይሆን ሀላፊነትን ለመሸከም ብቁ የሆነ የወጣት ትዉልድ ሳታቋርጥ ለማፍራት በመቻሏ ጭምር ነዉ:: በኢትዮጵያ የረዥም ዘመን ታሪክ ዉስጥ የተመዘገቡ የገድል ምዕራፎች ሁሉ የሚመሰክሩት ይህን ሀቅ ነዉ::

በተፃፈዉም ሆነ ባልተፃፈ ታሪካችን ዉስጥ እንደ ብርቅና ድንቅ የሚወሱት ጀግኖቻችን ለዚህም ክብርና ሞገስ ያበቃቸዉን ብሔራዊ ገዳጅ የተረከቡትና ያከናወኑት በወጣትነት ዕድሜአቸዉ ክልል ነዉ::ከቅርብ ግዜ ታሪካችን ምሳሌ ብንጠቅስ፤በፋሽስት ወረራ ስማቸዉ የገነነ አርበኞቻችን ወጣቶች ነበሩ:: እነ ጎሞራዉ÷ዘርዓይ ደረስ÷ጀጋማ ኬሎ÷በላይ ዘለቀ÷ ታከለ ወ /ኃዋርያት እነ ገረሱ ዱኪና ሌሎችም ዕልፍ አዕላፍ አርበኞቻችን ያኔ በዕድሜአቸዉ ወጣቶች የነበሩ ናቸዉ::

ኋላ ቀሩንና አድሎአዊዉን የፊዉዳል ሥርዓት ያንኮታኮተዉን ሕዝባዊ ትግል የመሩትና ትግሉ የጠየቀውን መስዋዕትነት ሁሉ ያለአንዳች ማመንታት የተቀበሉት አሁንም የኢትዮጵያ ወጣቶች ነበሩ::በኋላም አምባገነኑን ወታደራዊ ጁንታ ጉርምቦ ለጉርምቦ በመተናነቅ የታገሉት የኢትዮጵያ ወጣቶች መሆናቸዉን ለማረጋገጥ ታሪክ መጥቀስ አያሻም::ያልተረሳ የትናንት ትዝታ ነዉና::

የታሪክ ፍርጃ ሆኖብን የታገልነዉ የግፍ ሥርዓት ሲገረሰስ ተክቶብን የሄደዉ ሌላ ግፈኛና በይበልጥም ብሔራዊ ሕልዉናችንን አደጋ ላይ የጣለ ሥርዓት በመሆኑ ይህቺን ሀገር የማትረፍና ለብሔራዊ ሕልዉናችን ዋስትና የሚሆን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የማምጣት ኃላፊነት አሁንም በወጣቱ ትዉልድ ትከሻ ላይ የወደቀ ነዉ::

ይህ አባባል ዘበት አይደለም:: የፈጠጠ ሀቅ÷አማራጭ የሌለዉ እዉነታ ነዉ:: ይህችን ሀገር ለማዳን የወደቁትን ሰማዕታት ጀግኖቻችን ከመቃብር ወጥተዉ አይመጡልንም:: ወይም ሌላ የባዕድ ዜጋ ከባሕር ማዶ ገስግሶ አይደርስልንም:: ለመሆኑ የኢትዮጵያ ወጣቶች ይህን ሀቅ ምን ያህል ተገንዝበዉታል?

የኢትዮጵያ ባህልና በአጠቃላይ ህብረተሰብ ብቁና ሀገር ወዳድ ዜጎችን መፍጠር ፈፅሞ ተሥኖታል የሚል እምነት ባይኖርም ሀገሪቱ አሁን ከወደቀችበት ሥር የሰደደ ችግርና ችግሩ ከሚጠይቀዉ አጣዳፊ የትግል ምላሽ አኳያ ሲታይ ያሁኑ ወጣት ትዉልድ በአብዛኛዉ ከሃላፊነት የተዘናጋ ይመስላል:: ለመሆኑ ይህን በታሪካችን ያልተለመደ መዘናጋት በዚህ ትዉልድ ወቅት እንዴት ሊከሰት ቻለ? ጥያቄዉ አካዳሚክ ጥናትና ትንተና የሚያስፈልገዉ ቢሆንም ባጠቃላይ ግንዛቤ ያህል ወጣቱ ያለፈበትን የቅርብ ግዜ ታሪክና አሁንም እያለፈበት ያለዉን ፀረ- ሐገር ሥርዓት በመዳሰስ ለመመለስ እንሞክራለን::

አንድ ሰዉ በሐገር ጉዳይ ላይ ፀንቶ ለመቆም በመጀመሪያ ሀገሩን ማፍቀር ይኖርበታል::ብቃት ከሞላ ጎደል ከዚህ በኃላ ሊመጣ የሚችል ነዉ:: የሀገር ፍቅር ደግሞ በቅጽፈት የሚፈጠር ጉዳይ አይደለም:: ሀገር ወዳድ ዜጋ እንደ ባለሙያ በማሰልጠኛ ተቋም ሊመረት አይችልም:: ከትዉልድ ትዉልድ በተወረሰ ታሪክ ወግና ባህል ዉስጥ በማለፍ እንጂ:: ይህም የሚከናወነዉ ከልጅነት በሚጀምር ያስተዳደግ ሂደት(Upbringing and Socialization process ) አማካኝነት ነዉ:: እንደቤተሰብ የሃይማኖት የትምህርት ተቋማትያሉት ሥነ-ፅሑፍና ሁሉም የሥነ-ጥበብ ዘርፎች ማህበረሰቡ(Commnunity ) ወጣቱን በሀገር ፍቅር ስሜት ኮትኩተዉ ያሳድጉታል:: ከህብረተሰቡ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣዉን ታሪክ÷ወግና ÷ባህል ያወርሱታል:: ሀገሩ ስትደፈርና ክብሩ ሲነካ የሚያስቆጣዉን ወኔና ድፍረት በሕሊናዉ ዉስጥ ያስርጹለታል:: ለሀገር መሞትንና ለሀገር ቤዛ መሆንን የሞራል መሠረት ይጥሉለታል:: ጀግናን በማክበር÷ በማወደስና÷ በማሞገስ÷ በተፃራሪዉ

አድርባይን፥ፈሪንና አጎብጻጅን በመኮነንና በማንቋሸሽ ከህዲን በማዋረድና በማሳፈር በምሳሌነት የብቁን ዜጋ ስብዕና ይገነባሉ።

ባጭሩ እንድ ህብረተሰብ ተተኪዉን ትዉልድ በሀገር ፍቅር ኮትኩቶ ተንከባክቦና ለዚህ ፍቅር ፀንቶ መቆም የሚያስችለዉን የሥነልቦናና የሥነምግባር መሠረት መጣል ይኖርበታል።ህብረተሰቡን በሙሉ መተካትም ሆነ መወከል ባይችልም በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ይህን ኃላፊነት መወጣት ያለበት ደግም መንግሥት ነዉ። በሕዝቡ ሥም የሚሸከመዉ ሀገራዊ ኃላፊነት ስለሚኖርበት።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ላለፉት ሃያ ዓመታት ያለፉበትን አሁን እያለፉበት ያሉት የመንግሥት ሥርዓቶች ከላይ የተዘረዘረዉን ተቃራኒ ሂደት ሲያራምዱ የቆዩና የሚያራምዱ በመሆናቸዉ አሁን ወጣቱ ትዉልድ ላይ የሚታየዉ የላላ የሀገር ፍቅርና ስሜት ያለጥርጥር መንሥኤ ሆነዋል። ይህንንም እንደሚከተለዉ ዘርዝሮ ማብራራት ይቻላል።

1) ወጣቱ በደርግ መንግሥት ወቅት

<u>1ኛ/ ወጣቶችን ከሀገር ፍቅር ጋር የሚያስተሳስራቸዉን ማህበራዊ ያስተዳደግ ሂደት (Socialization process ) በአፍራሽ ፕሮፓጋንዳ መቀየሩ</u>

ደርግ ሥልጣኑን ባደላደለ ማግሥት ሃይማኖትን ጨምሮ ሁሉንም ማህበራዊና ባህላዊ ተቋማት በቁጥጥር ሥር አዋለ። የትምህርት፥የሥነጽሑፍ፥የትያትር፥የሙዚቃ፥የሲኒማና የመሳሰሉትን ተቋማት የሥርዓቱ የቅስቀሳና የፕሮፓጋንዳ ማምረቻና ማሰራጫ ማዕከሎች ሆኑ። ባለሙያዎች በፖለቲካ ካድሬዎች ተቀየሩ ወይንም ሙያቸዉን ርግፍ አድርገዉ ትተዉ እንደ ካድሬ እንዲሰሩ ተደረጉ።ይህ ግዳጅ የሃይማኖት አባቶችን እንኳ አላለፈም። ልጆች በእሥራት በስደት በመደበቅ፥....... ከሚያሳድጓቸዉ ከሚያስተምሯቸዉ በግድ ተነጡ። ይህ ማለት ደግም ወጣቶች ከትዉልድ የተወረሰዉን የወገንና የሀገር ፍቅር ለነፃነትና ለክብር ቀናዔ መሆንን ለመብት ተቆርቋሪነትን ወግና ባህልን ሥነ-ምግባርን የሚቀስሙትንና የሚለማመዱበት መንገድና በር ጥርቅም ብሎ ተዘጋባቸዉ ማለት ነዉ። ባሮጌዉ ምትክ አዲስ ታሪክ ወግና እንግዳ ባህል በመንግሥቱ ኃ/ማሪያም ብቻ ደፋርና አስተዋይ መሪ መንግሥቱ ብቻ ሁሉን አዋቂ መንግሥቱ ብቻ ሀገር ወዳድ መንግሥቱ ወይንም እሱ የመረጣቸዉ ነፍሰ ገዳዮች ብቻ መሆናቸዉን ለወጣቱ ይነገረዉ ጀመር።

ወገንን ለመጨፍጨፍ በግዴታ የተሰማራዉ ሠራዊት ነፃ አወጪ ዕልፍ አዕላፍ ወገኖችን ያረደና ቤት ንብረት ያወደመ ዘመቻ ሕዝባዊ ድል ንፁህን ዜጎችን በሞት የሚቀጣ ፍርድ ቤት የፍትህ ጠበቃ ወዘተ....... የሚል ስያሜ እየተሰጣቸዉ ወጣቱ ሀሰቱን እዉነት ጥፋቱን ልማት ቅጣቱን ሽልማት ብለህ እምን ዓይነት ግዳጅ ወደቀበት። ደራሲ ጆርጅ አርዌል 1984 በሚል ድርሰት አንዲት ሀሳባዊ ሀገር ፈጥሮ የዛችን ሀገር መሪ መፈክሮች የኮረጀዉ ከደርግ ሥርዓት ላይ ይመስላል።መፈክሮቹ የሚሉት እንዲህ ነዉ።

**War is peace!** (ጦርነት ሰላም ነዉ!)

**Slavery is freedom!**(ባርነት ነፃነት ነዉ)

**Ignorance is strength** (ድንቁርና ጥንካሬ ነው)

መንግሥቱ ኃ/ማርያም ወጣቱን ትዉልድ ያስተምረዉ የነበረዉ ትምህርት በተግባር ሲታይ ከዚህ ልበ -ወለድ ታሪክ የሚሻልበት ምንም ነገር የለዉም።

ደርግ ያን ያህል ቢደክምም የኢትዮጵያ ወጣት በሰላምና በጦርነት ፥ በባርነትና በነፃነት ፥በድንቁርናና በዕዉቀት መካከል ያለዉ ልዩነት ሊያደናግረዉ ባይችልም ከልጅነቱ ጀምሮ እየተኮተኮተ ሊያድግበት የሚገባዉ ከቤተሰብ ከማህበረሰብ ፥ ከትምህርትና ባህል ተቋሞች ከሥነ-ፅሑፍና ኪነት ሊያገኛቸዉ የሚገቡት ትምህርቶች አስተዳደጋዊ ዘዮዎችና ብሒሎች ዓርዓያ የሚያደርጋቸዉ ያባቶች ወግና ባህል የሀገረ ፍቅር ስሜት የጀግንነት መንፈስ ሥነ-ምግባር ወኔና ብርታት ተነፍጎታል፥ ማስተላለፊያዉ ቱቦ ተቆርጦበታል።ታዲያ ለዚህ ለደረሰዉ ከትዉልድ ወደ ትዉልድ የብሔራዊ ፀጋዎችን (virtues) በስርዓት መተላለፍ ወይም ሽግግር መቋረጥ ሰለባ የሆነዉ አዲሱ የዛሬ ወጣት ትዉልድ ሊከሰስበትና ለወቀስበት አይገባም።

2ኛ/ ፈሪነትና አንገት ደፍቶ መኖር መበርታቱ

የደርግ ርሕራሔ አልባ ጭፍጨፋና ፍጅት የተካሄደዉ በወጣቱ ላይ መሆኑን በዝርዝር ማስታወስ አያሻም ። ደሙ ያልደረቀ የትናንትና

ክስተት በመሆኑም ሁሉም ያስታዉሰዋልና:: ያሁኖቹ የኢትዮጵያ ወጣቶች በዚህ ሽብር ዉስጥ በጨቅላነትና በታዳጊ ወጣትነት ያለፉና ያደጉ ናቸዉ:: የዚያ ሽብር ዋና ዓላማ የወቅቱ ተቃዋሚን ለመመንጠር ቢሆንም ለተተኪዉ ትዉልድም ይህን ያየህ ተቀጣ የሚል መልዕክት ለማስተላለፍና/ ተከታይ ወጣቶች ፍርሃትን እንዲላበሱ ለማድረግ ነዉ:: ይህ ሽብር ያለጥርጥር የወጣቱን ስነ- ልቦና ሰልቦታል:: ታላቅ እህቱ ታለቅ ወንድሙ እናቱ ወይንም አባቱ ናላቸዉ በጥይት ፈርሶ ከበሩ ላይ ተጥለዉ ደማቸዉን ዉሻ እየላሰዉ እያየ ማልቀስ እንኳን የተከለከለ ወጣት መፍራትና አንገት መድፋት እንዴት ይነሰዉ! ደርግን ባደባባይ መቃወም ቀረቶ ሐሜት ያስገድል በነበረበት ሥርዓት ያደገ ወጣት "ቀን እስኪያልፍ ያለፋል" አጉል ብሒልን የህይወት መመሪያዉ እንዲያደረግ ተደረገ:: አዎ ያ ቀን አልፎአል መከራዉ ግን አላለፈም::መከራዉ ከዛሬዉ ቀን ጋር አብሮ መገፋት እንዳለበትና ይህም የወጣቱ ኃላፊነት ና ግዴታ መሆኑን አበክሮ የሚያስብበት የሚረዳበትና የሚያስላስልበት ፋታ አላገኘም ነበር::በለጋ አዕምሮዉ የቀረፀዉ አንገት በመድፋት ቀንን ማሳለፍ ነበር::

3ኛ/ አድርባይነት ሆን ተብሎ መበረታታቱ

በደርግ ዘመን የሙያ ብቃት ዕዉቀትና ሀቀኝነት የተናቁበትና በተቃራኒዉ ሥልጣን ሃብትና የተደላደለ ኑሮ ለሥርዓት ከማጎብደድ ጋር የተያያዙ የአድርባዮች ይዞታ ሆነዉ ነበር::የሥራ ቦታዎች የቴክኒክና የሙያ ብቃት የሚጠይቁትን ጨምሮ ባልተማሩ መኮንኖችና ካድሬዎች የተያዙ ነበሩ:: ወጣቱ ሙያና ብቃት ለጊዜዉ የትም እንደማያደርሱና ይልቁኑም ሥርዓቱን በመደገፍና በማገልገል የተሻለ ኑሮ መኖር እንደሚቻል አይቷል፥ ሰምቷል፥ ይህንኑ ቅርናት እየታወደበት አድጓል::

አብዛኛዉ የሀገሪቱ ሀብት በመንግሥት ይዞታ ሥር ስለወደቀ ሥራ፥ ራሽንና መሰረታዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሥርዓቱ ደጋፊ መሆን ግዴታ ነበር:: ከአኢወማ፥ ከአኢሴማ፥ መኢገማ፥ መኢሠማ፥ከነማ፥ ኢሠፓ መሠረታዊ ድርጅት ዉይይት ክበብ ወዘተ የድጋፍ ማረጋገጫ በመንፈግና በመስጠት የግዳጅ ተሣትፎን ያረጋግጣሉ:: መንግሥት ወይንም እነዚህ ማህበራትና አካላት ከጠሩት ስብሰባ፥ ዘመቻ፥ ሰላማዊ ሰልፍ፥የናትሀገር ጥሪ፥ ባዛር፥ መዋጮ፥ ኪነት ወዘተ....... መቅረት በትንሹ እራሽን ያስከለክላል::

የአኢወማን ድጋፍና ደብዳቤ ያልያዘ ኮሌጅ ተመዝጋቢ ከመማር ዕድሉ ይታገድ እንደነበረ ሁላችንም ያልረሳዉ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነዉ::የብሔራዊ ዉትድርና አገልግሎት የፈፀመ ማንኛዉም ወጣት ኮሌጅ ለመግባት የመግቢያ ነጥብ ወይም መመዘኛ ማሟላት አያስፈልገዉም ነበር:: ተመርቆም ሆን ሳይመረቅ ለመያዝ ማመልከቻ ሲያቀርብ የአኢወማ የድጋፍ ደብዳቤ ከሌለዉ ሥራ አያገኝም::ዝርዘሩ/ ብዙ ነዉ ባጭሩ ግን ይህ አዲስ ትዉልድ የሚጠላዉን ስርዓት ደግፎና ግፍ ሲሰራ አጨብጭቦ መኖር እንደሚችል ነዉ:: እያየ ያደገዉ::

በአጠቃላይ ወጣቱ ባለፉት የደርግ አገዛዝ አመታት ዉስጥ ከመጨፍጨፉ ከመታሰሩና በግዳጅ ዉትድርና አገልግሎት እንዲሰማራ ከመገደዱ አልፎ የሽፍጥና የዉሸት ኑሮ እንዲገፋ ተደርጓል:: እያየ ያደረገዉ ሁሉ ሀገሩን የሚያስጠላ እንጂ የሚያስወድድ አይደለም:: የማያዉቀዉን የባዕድ ሀገር የሚያስናፍቅ የሥደት የተዋርዶ ኑሮ እፁብ ድንቅ የሚል ዜጋ ሊፈጠር የቻለዉ በዚህ የጥፋት ሥርዓት ተፅዕኖ መሆኑ መዘንጋት የለበትም::

ይህ በግፍ ዘመን ተወልዶ በግፍ ሥርዓት ያደገ ወጣት ትዉልድ የደርግ መገርሰስ መከራዉን በቃህ አላለዉም::የባሰ የጨለመና ተስፋ የሚያስቆርጥ የጎሣ አምባገነን ሥርዓት ተተካበት:: ያለፈዉ የፖለቲካ ሽብር የወያኔን የኤኮኖሚ ሽብር ጨምሮ ብቅ አለበት:: ስለ ጎሣዉ እንጂ ስለ ሀገሩ እንዳያስብ ተደረግ:: ወጣቱ ትዉልድ ባሁኑ የወያኔ ሥርዓት ዉስጥ የተጋረጠበትን ችግር እንደሚከተለዉ ዘርዝሮ ማየት ይቻላል::

4ኛ) ወጣቱ በወያኔ ሥርዓት ዉስጥ

በበቂ የተደራጀና የተጠናከረ ስለዚህም ቀጣይነትን ያረጋገጠ ባይሆንም ወያኔም እንደደርግ የመረረ ተቃዉሞ የገጠመዉ ከወጣቱ ህብረተሰብ ጭምር በመሆኑ ዱላዉን ያሳረፈዉ በወጣቱ ላይ ነዉ:: ብዛት ያላቸዉ የወያኔ ተቃዋሚዎች እንደሚሉት ወያኔ ማዕከላዊ የሀገሪቱን ግዛት በተቆጣጠረበት ወቅት ከአካባቢዉ ህዝብ ድጋፍ አግኝቶ ነበር የሚለዉ አባባል ፈፅሞ ከእዉነት የራቀ ነዉ:: የሕዝቡን ተቃዉሞ በኃይል እየጨፈለቀ ነበር ወደ አዲስ አበባ የገሰገሰዉ::

ወያኔ ከተሞችን እንደተቆጣጠረ ባሕርዳር፥ ጎንደር፥ ደብርማርቆስና ፥ደሴ ከተሞች የተነሱ የተቃዋሚ ሰልፎች ላይ የተረሸኑት ወጣቶች አስከሬን እንዳይቀበር በወያኔ ነፍሰገዳዮች ተከልክሉ ከጨለመ በኋላ ወላጆች አንስተዉ እንደቀበሩ የነዚያ ከተሞች ሕዝብ የማይረሳዉ ግፍ ነዉ። አምቦ ላይና ከዚያም አዲስ አበባ ከተማ ዉስጥ የተካሄዱተን ቀጣይ ጭፍጨፋዎች . እንዳናስታዉሰ. ያደረገን ወያኔ ከዚያ በኃላ በወሰዳቸዉ መጠነ ሰፊ ጭፍጨፋዎች ስለተለወጡ ነዉ። በእነዚህ ሁሉ ተቃዉሞዎች ግንባር ቀደም ተሳታፊዎች ወጣቶች ነበሩ። ወያኔ የትግራይ ነፃ መንግሥት የማቋቋም ዓላማዉን በጊዜያዊነት ገታ አድርጎ መላዉ ኢትዮጵያን በመቆጣጠር ላይ ከተሰማራበት ዕለት ጀመሮ ከኢትዮጵያ ወጣቶች ሊገጥመዉ የሚችለዉን ተቃዉም በሚገባ አሰቦበት ስለነበር ስትራቴጅክ ፀረ- ወጣት ፖሊሲ አዘጋጅቶ እንደመጣ ከተግባሩ መረዳት አያዳግትም። ወጣቱን ደርግ እንዳደረገዉ ሁሉ በመግደል፥ በማሰርና በመግረፍ ከማስፈራራት ዉጭ በጎሣ መከፋፈልና ማናቆር እንደዋነኛ ማዳከሚያና ተስፋ ማስቆረጫ ዘዴዉ አድርጎ ይዞታል። ህገራዊ ስሜቱን ንቃተ- ህሊናዉንና ግንዛቤዉን ታሪኩን.... ለማጥፋትና ለማፍለስ ጠባብ ብሔረተኛ ስሜትን እያራገቡ ርስ -በርስ በማቃቃርና በማፈራረቅ ባንድነት እንዳይታገላቸዉ ለመበታተን ያልተቋረጠ ዘመቻ እያካሄዱበት አሁንም ቀጥለዋል።

ወያኔ ሥልጣን እንደያዘ በቅድሚያ የጀመረዉ የፖለቲካና ድርጅታዊ ሥራ ወጣቶችን "የወጣት ኮር" በሚል ስም በማህበር መልክ ማደራጀት ነበር "የወጣት ኮር" እየተባሉ የተሰበሰቡት ወጣቶች "ክፍለህዝቢ" በሚል መጠሪያ በሚታወቁት የወያኔ ካድሬዎች አደራጅነትና ሰብሳቢነት ፀረ-አንድነት የሆነ የብሔረሰብና የጎሳን ጥላቻን መርዝ ይግታሉ። በመጀመሪያዎቹ ዓመታት የሚመለመል ወጣት በመጥፋቱ ወያኔ በደርግ ሥርና ዉስጥ ሆኖ የተማረዉን አድር ባይ ክፍል መሳቢያና መመልመያ ስልት ቀይሰዉ ነበር። ይኸዉም በርካታ ሰዎች ከሥራ እየተባረሩ በነበሩበት ወቅት ሥራ መስጠትን በተመለከተ ከሁሉም ቅድሚያ ለኮር አባላት ይሰጣል የሚል መመሪያ ነዉ። ወያኔ የቀጠራቸዉ በብዙ ሺህ የሚቀጠሩ አዲስ ፖሊሶች የግብርናና የተፈጥሮ ሀብት መሥሪያ ቤቶች የኤክስቴንስን ሰራተኞች በገበሬዉ ዘንድ የወያኔ ካድሬዎች በመባል ነዉ የሚታወቁት። በወረዳ በዞንና በክልል ደረጃ የሚገኙ አብዛኛዎቹ የመሥሪያ ቤት ኃላፊዎችና ሠራተኞች ከወጣት ኮር የተመለመሉ ናቸዉ።

የወያኔ የጠባብ ብሔረተኝነትና የጎሰኝነት መርህ በየትኛዉም የህብረተሰብ ሕይወት ዉስጥ እንዲስፋፋ ስር እንዲሰድድ እንዲራመድ ያልተቋረጠ ጥረት ተደርጓል። በዚህ መርህ መሰረት ሁሉም ብሔረሰቡን ጎሳዉን እንጂ ህገሩን ማወቅ ማልማት መከላከል ማፍቀር ወዘተ... የለበትም ። የልማት ማህበራትና የስፖርት ክለቦች ሳይቀሩ በብሔረሰብና በጎሳ ላይ ተመስርተዉ ተደራጅተዋል። በተፃራሪዉ ህብረ-ብሔራዊ የሆነዉ ህገራዊነትና የኢትዮጵያ አንድነት የተባሉ ፅንሰ -ሃሳቦች በወጣቶች ህሊና ዉስጥ እንዳይቀረፁ ወያኔ በሩን ሁሉ በጥንቃቄ ለመዝጋት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። በአብዛኛዉ የህገሪቱ ክፍል የህገሪቱ ሰንደቅ ዓላማ ወርዶ በምትኩ የክልል አርማ ነው የሚዉለበለበዉ።ጧትና ማታ ሰንደቅዓላም አይወጣም አይወርድም።ብሔራዊ መዝሙር የሚባለዉ በወጣቶች ዘንድ ፈጽሞ አይታወቅም። ጀግኖችና የጀግንነት ታሪካችን አይወሳም እንዲያዉም ለህገር አንድነት ና ለህገር ነፃነት የተዋደቁት ጀግኖች ይዘለፋሉ ይኮነናሉ ይወገዛሉ። ይህ ለምሳሌ ያህል ተጠቀሰ እንጅ በሁሉም የህብረተሰብ ሕይወት ህገራዊነት እንዳይነግስና ጎሰኝነትም ቦታዉንም እንዲይዝ በወያኔ የሚደረገዉ ጥረት በዝህች አጭር ፅሑፍ ዉስጥ ተዘርዝሮ አያልቅም። ከዚህ ተነስቶ ግን አንድ ነገር ማለት ይቻላል ።ይኸዉም ወያኔ ይህን ወጣት ትዉልድ ህገሩን ፈጽሞ እንዳያዉቅና እንዳይወድ እንዲያዉም እንዲጠላ የሥነ- ልቦና ዘመቻዉን እያጠናከረ መሆኑን ነዉ። ከደርግ ሥርዓት ጀምሮ እየተሸማቀቀ እየተዋከበና ግራ እየተጋባ የመጣ ወጣት የህገር ጉዳይ ቋ ጠሮ ዉሉ ቢጠፋበት የሚያስደንቅ አይሆንም ። በዚህ ጽሁፍ መጀመሪያ አካባቢ እንደተገለጠዉ ማንም ሰዉ ቢሆን ህገርወዳድ ሆኖ አይወለድም። ወኔ ጀግንነትና የታማኝ ባላደራነት ሥነ- ምግባር ያስተዳደግ ሂደት ዉስጥ የስብዕና አካል እየሆኑ የሚያድጉ መሆናቸዉን ልንዘነጋ አይገባንም ። ስለዚህም ነዉ አዲስና ትኩስ የሆነዉ ወጣት የተደቀነበትን አሸከላ ምክኒያት በመረዳት የዛሬዉን ችግር በጋራ ለመፍታት የወደፊቱን ሁኔታም ለማሻሻል ሃላፊነቱን ተገንዝቦ መነሣት የሚጠበቅበት።

ሁለተኛዉ የወያኔ ፀረ-ወጣት ዘመቻ በኤኮኖሚ ሸብር የሚጠቃለል ነዉ።የሥራ ዕድል ከሞላጎደል ሞልቷል ።ዲግሪና ዲፕሎማ በደርግ ጊዜ እንኳ ይዘዉት የነበረዉን ሥራ ለማስገኘት

ዋስትና አሁን አጥተዋል ::ወደዉም ሆነ ተገደዉ ለወያኔ መሣሪያነት አሁን ከተዳረጉት በሕወሓትና በተለጣፊ ቡድኖች አማካይነት ከተሰባሰቡት በርካታዎቹ የትግራይ ትግሪኝ ተወላጅ ከሆኑ ወጣቶች ዉጭ የሥራ ማግኘት ዋስትና ያለዉ ወጣት የለም:: በሺህ የሚቆጠር ሠራተኛ ሕዝብ ከሥራ ሲባረር በገፍ መባረሩ የመኖር ተስፋ መጨለምን በማስከተሉ ኤኮኖሚያዊ ሽብሩን አባብሶታል:: በመማርና ባለመማር ያለዉ ልዩነት በተማሩ ሥራ አጦች መጨመር ምክኒያት ጠፍቷል ::ችግሩን ይበልጥ ለማባበስ ደግም ትምህርት በክፍያ እንዲሆን አዲስ መመሪያ ወጥቷል:: ወጣቱ ይህንን ግፍ በሰላማዊ መንገድ ለመታገል አልቻለም :: ባዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሠላማዊ ሰልፍ ተሣታፊዎች ላይ የደረሰዉን ግድያና በየኮሌጁና በየሁለተኛ ደረጃዉ ትምህርት ቤቶች ዉስጥ ነቃ ነቃ ባሉ ተማሪዎች ላይ የደረሰዉን አፈሳና እንግልት አይቷልና::

ዛሬ ወጣቱ ተስፋዉ ጨልሞበታል÷ ጠዉልጎበታል::ስለወደፊት ሕይወቱና ስለሀገሪቱ የወደፊት ዕጣ ፈንታ አይጨነቅም ባንልም አቋም ለመዉሰድና አምርሮ ለመታገል የሚያስችለዉን የስነ ልቦና ጥንካሬ ገና መቀዳጀት ይጠበቅበታል:: እፊቱ ላይ ከተደቀነዉ አስፈሪ ዉነታ ለመራቅ ስደትን ሱሰኝነትን ሴሰኝነትንና የባዕድ ባህልንና አምልኮን እንደአማራጭ ሲጠቀምበት ይታያል:: ወያኔ ደግም እነዚህን እኩይ ልምዶች ሆን ብሎ በማበረታታት ላይ ይገኛል:: የወጣቱን ሀገራዊ ስሜት÷ ነፃነት ወዳድነት÷ ለመብቱ ተቆርቋሪነትና ፖለቲካዊ ተሳትፎን ያዳክምልኛል ብሎ የሚገምተዉን ነገርና ክስተት ፈሊጥና ባህል ልምድና ሱስ እምነትና ተግባር ሁሉ ወያኔ እንደ አጋርና ረዳቱ ነዉ የሚቆጥረዉ::

ለዘመናት ተዘግተዉ የነበሩ ድንበሮች በራቸዉ በሰፊዉ ተከፍቷል:: በሞትና በእስራት ሊቀጡት የሚፈልጉት ወይም በዓይነቁራኛ ሊጠብቁት የሚሹት የሥርዓታቸዉ ተቃዋሚ ካልሆን በስተቀር ማንኛዉም ዜጋ ወደ ጎረቤት ሀገር ለመሰደድ ቾግር አይገጥመዉም :: የወያኔ ኬላ ጠባቂዎች አትመለስ አንጂ ዉጣ እያሉ የሚሸኙ ነዉ የሚመስሉት:: ሀገሪቱ ዉስጥ የሚቀረዉ ደጋፊያቸዉ ክፍል ብቻ እንዲሆንላቸዉ የሚመኙም ይመስላሉ:

ወያኔ የወንጀልና የወሲብ ፊልሞችን በገፍ እንዲገቡ በሩን ከፈቶ እያበረታታ ነዉ:: ከትግራይ ዉጭ ባሉ የሀገሪቱ ክፍሎች የቪዲዮ ፊልም ማሳያ ንግድ ቤቶች እንደ አሸን ፈልተዋል:: የንግድ ፈቃድ አይጠየቁም::የሚያሳዩት ፊልምም ይዘት አይመረመርም ::በሌላዉ ዓይነት ንግድ ለሕዝቡ ሕይወት አስፍላጊ የሆኑትን ሸቀጦችና አገልግሎቶችን በማቅረብ ላይ የተሰማሩትን አዙዋሪዎችን ለፍቶ አዳሪዎችን ግን ያዋክባሉ ይቀማሉ ይደበድባሉ ያስራሉ ይገድላሉም:: የሀገራችን ወጣቶች ወደ ጥፋት የሚያመሩ ከበለፀጉ ሀገሮች የሚቀናጣዉን አነስተኛ ክፍል ባህሎች ለወጣቶቻችን በገፍ እያቀረቡላቸዉ ነዉ:: ወጣቶች በራሳቸዉና በወላጆቻቸዉ አቅም ሊያገኙት የማይችሉትን የቅንጦት አኗኗርና ዘይቤ እንዲለምዱ÷ እንዲጠመዱበት ከባህላችንና ከኤኮኖሚያዊ የዕድገት ደረጃችን አኳያ ደግሞ ሲታይ አስነዋሪ ከመሆኑም በላይ አሸመድማጅና አጥፊ በሆነ ልማድ እንዲገዙ እየተደረገ ነዉ:: ኑሮዉን ለመልመድ ወንጀል መሥራትና መስሎ ለመታየት የቀን ህልም የሚያልሙ "ፈሪኮች" ከተሞችን እየሞሉ ነዉ:: ያደንዛዥ ዕፅ የጫት የአልኮልና የዝሙት ችግሮች ወጣቱን እያዳረሱት እያናወዙትና ወኔዉን ም በተወሰነ ደረጃ ቢሆንም እየሰለቡት ይገኛሉ::

ከዚህ ለተረፈዉ ወጣት አዳዲስ የባዕድ አምልኮዎች እንደሸቀጥ በገፍ እየገቡለት ነዉ:: በዚህ መስመር የተጠቃለሉ ወጣቶች ደግም ለመብትና ለክብር መፋለምን በደልና ግፍን መቃወምን ለህብረተሰቡ የወደፊት ኑሮና ሕይወት መጨነቅን በጠቅላላም ፖለቲካን እንደ መርዝ እንጠላለን በሚል ሰበብ በሀገር ጉዳይ ላለመሳተፍ የወሰኑ ይመስላሉ:: ከሃላፊነት ለመሸሽ ፍርሃትንና ወኔ- ቢስነትን ለመሸፋፈን ካልሆነ በስተቀር ባርነትን አሜን ብለህ ተመልከት የሚል ትምህርት (doctrine )ያለዉ የዕምነት መጽሐፍ ያለ አይመስለንም ::መጽሐፍ ቅዱስና ቅዱስ ቁርዓን ሀገራችንን እንድንወድና እንድንጠብቅ ነዉ የሚያስተምሩን:: መጽሐፈ እያሱ ሙሉ መጽሐፉ የሚያስተምረን ሀገርን እንድንወድ እንደንጠብቅና ለነፃነቷ ጦር መዘን እንድናዋጋ ነዉ::

በአጠቃላይ የወጣቱ ችግር ውስብስብና ሥር የሰደደ በመሆኑ ይህን ትዉልድ የሚወቅሱ ሀያሲያን ሁሉ የችግሩን መንስዔም አብረዉ ሊመረምሩት ይገባል:: የወጣቱ ትዉልድ ችግር ከሞላ ጎደል ይታወቃል::ብዙ ተብሎለታል ምንም ያልተባለለት መፍትሄዉ ነዉ::ይ.ህንን ችግር እንዴት እንወጣዉ? ለዚህ ጥያቄ አጭርና ቀላል መልስ የለዉም :: ሆኖም ሁሉም ተቆርቋሪ ወገን የመሰለዉንና ያቅሙን ካበረከተ ወደ መልሱ መቃረብ ይቻላል:: ይህች ጽሑፍ የበኩሏን

መላ እንደሚከተለዉ ለማማመልከት ትሞክራለች::

በመጀመሪያ ደረጃ አብዛኛዉን ሀያሲያን እንደሚሉት ወጣቱ ላይ የሚታየዉ የሀገር ፍቅር መላላት ወኔ ማጣትና በሱስ መለከፍና መጠመድ ሙሉ በሙሉ ተስፋ በሚያስቆርጥ ጀረጃ ላይ አይደለም:: ሲወርድ ሲዋረድ በመጣዉ የጀግና ትዉልድ ሰንሰለት ሙሉ በመሉ ይቋረጣል ለማለት አይቻልም:: በቁጥር በጣም ይነሱ እንጂ አሁንም ጠንካራ የሀገር ፍቅር ያላቸዉ በወገናቸዉና በራሳቸዉም ላይ የሚደርሰዉ በደል የሚያስቆጣቸዉ ግፍና ጭቆናን የሚቃወሙ ምሬታቸዉንም በትግል ለመግለጥ ወኔዉ ያላቸዉ የተወሰኑ ወጣቶች በየከተሞች ዉጥም ይገኛሉ :: በሚሊዮን የሚቆጠርና ያልተበከለ ጤናማ አስተሳሰብ በሳል የሆነ አዕምሮና ለተለያዩ ሙያዎች ዝግጁነት ያለዉ ድንግል ወጣት በአብዛኛዉ የሚገኛዉ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ዉስጥና በትንንሽ ከተማዎች ማለትም ብክለት ባልተስፋፋባቸዉ ስፍራዎች መሆኑ መረሳት የለበትም:: ይህ ወጣት በአብዛኛዉ ከወያኔ ቁጥጥር ዉጭ ከመሆኑም በላይ በአፍዝ አድንግዝ ዕጾች ያልተበከለ በሌሎች አልባሌ ልምዶችም ያልተጠመደ ነዉ:: አብዛኛዉም ወኔ ያልከዳዉና ሀሞተ- ኮስታራ ነዉ ማለት ይቻላል:: -

ከዚህ በተጨማሪ የወያኔ ፀረ- አንድነት ፕሮፓጋንዳ ካንድነት ኃይሎች ደጋፊዎችና ምሁራን ከሚደርስበት ወገናዊ ምላሽ የተነሳ በፖለቲካ ትግሉ የራሱን ደካማ ሀሳቦች በበቂ ሊከላከል ከቶዉንም አልቻለም:: እንዲያዉም በዋለና ባደረ የፖለቲካ አቋሞች ጎጂነት በግልፅ እየታየ በመምጣቱ ወያኔም ጠቃሚነታቸዉን ለማሳመን የማይችል መሆኑን እየተረዳ ተስፋም እየቆረጠ በጉልበት ብቻ ለመያዝና ለመግዛት ለማስፈራራት በመጨቆንና በማመቅ በማሰር አለዚያ በመግደል ላይ ሕላዌዉ የሚንጠለጠልበትን ሁኔታ እየፈጠረ ነዉ::

ስለዚህ ወጣቱ ከሀገር ጉዳይ ሀሳብና ጭንቀት ጭራሹን በሙሉ ተገልሏል÷ የሀገራችን የሕዝባችን ተስፋም ተመናምኗል የሚለዉ ተስፋ መቁረጥ መሰረት የለዉም::

በሁለተኛ ደረጃ ወጣቱ ታሪክ የጣለበትን ኃለፍነትና ግዴታ እንዲወጣ ማስተማር ባልባሌ ጎጅ ነገሮች የተጠቃዉንም ክፍል እየመከሩና እያበረታቱ ማዳን ጤናማዎቹንና ከመጥፎ ልምዶች ሊላቀቁ የቻሉትን ሳይጣደፉና ሳይታክቱ ደረጃ በደረጃ ማደራጀት የሚታገሉላቸዉን ዓላማዎች መተክሉች ፖሊሲዎችን አቋሞች ማስረዳትና ማስጨበጥ ታክቲክና እስትራቴጂ ቀይሶ ማታገል ያስፈልጋል:: እንደሚታወቀዉ በሀገራችን ህጋዊ በሆነ መንገድ ስሰለሀገር ጉዳይ ነፃ ሆኖ መወያየትም ሆነ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መታገል አይቻልም:: የሕዋሓት/ ኢሕአደግ አምባገነናዊ አግዛዝና ሥርዓት ሰፍኗል:: ስለዚህ ወጣቱ ተነጣጥሎ ነዉ ያለዉ :: በዚህ ሁኔታ ላይ ያለ ወጣት ደግም ብሶቱ ከልክ ሲያልፍ ግብታዊ ቁጣ ከማሳየት በተናጥልም ከመመታት ከመታሰርና ከመገደል ዉጭ ዘለቂ ዉጤት ሊአመጣ አይቸልም :: ይህን የዚያ አይበገሬ ትዉልድ ታሪክ አረጋግጦልናል::ያኔ በተለይ ከ 1966 ዓ.ም. ጀምሮ ኢሕአፓ ወጣቱን በስፋት አደራጅቶ በቂ የሥነ-ልቦና መሰረት ጥሎ በዲስፕሊን አንፆ ታክቲክና ስትራቴጂ ነድፎ በዕለት -ተዕለት አመራር እየሰጠ ነበር ወጣቱን ያታገለዉ:: ሞትን ሰቆቃን ግርፋትን ርሃብን እርዛትንና ድካምን የማይፈራ ለዓላማዉና ለቃሉ የፀና ባጠቃላይ የጀግንነት ሥነ- ምግባር የተዋኸደዉ ወጣት የተፈጠረዉ በድርጅቱ ጥረትና በአደራጂዎች ጥንካሬ መሆኑን መጠራጠር አይኖርብንም::

የሰብል ፍሬ እንደዘሩ ዓይነተኛ ጥራት እንደ መሬቱ ልምላሜ እንደገበሬዉ እዉቀትና ታታሪነት ይለያያልና ባሁኑ ትዉልድ ላይ የምንዘራዉ የአንድነት የሀገር ፍቅር የነፃነት አፍቃሪነት የመብቱ ጠባቂነት መንፈስና ጽናት ዉጤቱ እንዳለፈዉ ጊዜና ትዉልድ ጉልህ አመርቂ አይሁን እንጅ ከብዙ በጥቂቱ ብቁ ወጣቶችን አሁንም ለማፍራት እየተቻለ ነዉ:: በተጠናከረ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ሥራ በርካታ ብቁ ንቁ ቆራጥና ፅኑ ወጣቶችን ዛሬና ነገም ለማፍራት የማይቻልበት ምንም ምክንያት የለም:: ስለዚህ የአንድነት ሀይሎች ሁሉ ይህን የቅርብ ጊዜ ታሪካችንን ተመክሮ በተግባር በመተርጎም ወጣቱን በሚስጢር በትንሽ በትንሹ እያደራጁ ካላታገሉት ለጠቅላላ ዕዉቀት በሚወጣ የጋዜጣ ምክር የሚመጣ ህውፌ እምብዛም አይኖርም :: አፍ-ለአፍ ሰዉ- ከሰዉ እየተገኙ መነጋገር ሃሳብ ለሃሳብ መለዋወጥ መወያየት መከራከር መተማመንና የሃሳብ አንድነትን ወይም መቀራረብን ለመፍጠር ያለማቋረጥ መጣር ያስፈልጋል :: በሃሳብ አንድነት / ተቀራራቢነት ላይ ተመስርቶ ነዉ ለተወሰኑ የጋራ ዓላማዎች አብሮ ለመሥራት በድርጅት ለመሰባሰብ አብሮም ለመታገል የሚቻለዉ::

ሦስተኛ÷ የሰዉ ባህሪ በተራዘመ ማህበራዊዉ ሂደት የተለያዩ መንገዶችን

ማለት- እንደ ታሪክ ትዉኔት ሥነ-ፅሑፍና ሌሎች የኪነጥበብ ዘርፎችን በመጠቀም የሚቀረፅ በመሆኑ በደረቅ ምክርና ቀጥተኛ ቅስቀሳ ብቻ ሁሉም ሁልግዜና በፍጥነት የሚለወጥ አይሆንም። የዚህ ዓይነት አቀራረብ ለተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችና ቡድኖች ሊሰለች ከመቻሉም በላይ በአርዕስቶቹ ላይ ጥላቻንም ሊፈጥር ይችላል ስለዚህ በምሳሌነታቸዉ የሚያስተምሩ የጀግና ወይንም የፈጠራ ሥራዎችን ለወጣቶች ለማዳረስ እንዲጥሩ አማራጭ መንገዶችን ሊፈልጉ ይገባል ። በተለይ ለሕዝብ የሚሰራዉ የፕረስ ዉጤቶች ሙዚቃ መፃህፍት ወዘተ... ወጣቱን ለማስተማር አቀራረባቸዉን ስህበትና ማራኪነት ያላቸዉ በማድረግና ለወጣቱም እንዲደርሱ ለማድረግ መጣር አለባቸዉ። የሥነጽሑፍ የኪነት የእስፖርት እንቅስቃሴዎችና ማህበሮች ወጣቱን አቅጣጫ በማስያዝ ትልቅ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ።

አራተኛ፥ እየተስፋፋ ያለዉ የአደንዛዥ ዕፅ ፥ የወሲብና የጎጂ የሱስን ባህል ሙሉ በሙሉ ለመከላከል የመንግሥት ትብብር እንደማይገኝ አዉቆ የእስፖርት የባህል የሃይማኖትና የትምህርት ተቋማት ጥረቶቻቸዉን እንዲያጠናክሩ በተገኘዉ መድረክ ሁሉ መገፋፊት ያስፈልጋል።

በመጨረሻም ወጣቶች እራሳቸዉን ለመለወጥ ጥረት ማድረግ አለባቸዉ።የአፍዝ አደንግዝ ዕፆች ሱስ ያልኮል መጠጦች ሱሰኛና ሰካራም መሆን ሴሰኝነት የተላያዩ ፊር-አሳቹ መጤ ዕምነቶች ሠለባ መሆን ....የወጣቱን በሀገሩና በወገኑ ችግሮች ላይ እንዳያተኩር ሀገራዊ ቅርሶቻችንና ፀጋዎች የሆኑት ባህርያት ዕምነቶችና ስሜቶች እያሳሱት እያዳከሙት በቀላሉ የሚረታና የሚቸነፍም እያደረጉ ናቸዉ።ወቅቱ ሐገር በጣዕር የተያዘችበትና ሕልዉናዋ አደጋ ላይ የወደቀበት በመሆኑ መከራዋን ተካፍለን ችግሯን ተቸግረን ልንታገልላትይገባል እንጂ የማናገኘዉን የቅንጦት ሕይወት የምንመኝበት አይደለም።ፖለቲካን ጠላሁ በሚል ሰበብ ኃላፊነት መሸሽ ወይም ሀገር በእሳት ስትነድ ባዕድ መጥቶ ያጥፋዉ በሚል ጭፍን ፍርሃት ሃገር ጥሎ መሰደድ እንደ "ጂብሲ" ሀገር የለሽ ከርታታ ሆኖ መቅረትን ያመጣል ወይም እንደፍልስጤሞች በሀገሩ ስደተኛ ከመሆን ማምለጥ አይቻልም።

ነፃነትና ብሔራዊ ሉዓላዊነት በዜጎች ትግልና መስዋዕትነት ብቻ ነዉ ተጠብቀዉ የሚኖሩት። ይህን መስዋዕት ለመክፈል የተዘጋጀ ትዉልድ በሌለበት ወይንም ባነሰበት ወቅት ነፃነትና ሉዓላዊነት እንደአከረፈ ዉቃቢ ቀስ ብለዉ ከዜጎች እጅ ይወጣሉ። በምትካቸዉ ባርነትና ተገዥነት ቦታቸዉን ይይዛሉ። ይህ ትዉልድ ለአፍታም ቢሆን ሊዘነጋዉ የማይገባ ይህ እንደ ተረት እየሰማነዉ ያለዉ ሀገር የማጣት ፍርሃት እዉን እየሆነና እየቀረበ መምጣቱን ነዉ።አሁንም የምንኖረዉ በተሸፋፈነ ባርነት ነዉ የምንገፋዉ የጉስቁልናና የዉሸት ሕይወት ነዉ። ከዚህ በላይ የሚያስፈራ ነገር አይኖርም። በመታገል የምናጣዉ አንዳችም ነገር የለም።እንዲያዉም ታጋይ ነፃነቱን ያወጀ በመሆኑ ሕይወቱ የመንፈስ ሰላም የሰፈነበትና የሚኖረዉም የኩራት ሕይወት ነዉ ለነፃነት ለመብትና ለክብር የሚፋለም ወጣት ከሁሉም በላይ የገነባዉን ብሩህ ተስፋ አልፎም የሚንዝ በመሆኑ የደስታ ኑሮ ይኖራል። ከፍርሃትና ከጭንቀት ነፃ ነዉ። ሞት ሰቆቃ እስራትና ግርፋት ታጋይን ቢያንስ ተረግጦና ተዋርዶ አጎብድዶና እየቀላመዱ የመኖርን ያህል አያስፈሩትም ።ስብዕናዉን አይቀንስበትም። ለነገሩ በሰላማዊ ግዜ በጨቋኝ አምባገነንነትና አማቂ መንግሥት ቀስበቀስ እየተለቀሙም ሆን አንዳዴም በሚደረጉ ጭፍጨፋዎች የሚያልቀዉ ሠላማዊ ሕዝብ ብዛት በጦርነት አምባገነኑን መንግሥት በትጥቅ ጭምር በመፋለም ሊያልቅ ከሚችለዉ ሠላማዊ ሕዝብና ታጋይ ቁጥር ምንግዜም አንሶ አያዉቅም ባጭሩ ፊርቶ መቀመጥ በጠላት ከመገደል ከመታሰርና ከመገረፍ አያድንም ለማለት ነዉ።

ለማጠቃለል በዚህች ጽሑፍ መጀመሪያ አካባቢ የተባለችን አንድ አባባል ልንደግመዉ እንወዳለን።

ይህችን ሀገር ለማዳን የወደቁት ሰማዕታት ጀግኖቻችን ከመቃብር ወጥተዉ አይመጡሉንም ወይም የባዕድ ዜጋ እኛን ለማዳን ከባህር ማዶ ገስግሶ አይደርስልንም። ባለተርታ-ተራ የታሪክ ተረካቢዎች የሀገር ባላደራዎች እኛዉ ዛሬ በወጣትነት ትዉልድ የዕድሜ ክልል የምንገኘዉና ከእኛ ቀደም ካለዉ ትዉልድ ደግም ከመስዋዕትነት ተርፎ አሁንም ለሀገሩ አንድነት ለሕዝቦችዋ እኩልነት ለነፃነቱ ለመብቱና ለክብሩ ለዴሞክራሲ ........ በመፋለም ላይ የሚገኘዉ ዓርአያም እየሆነን ያለዉ ክፍል ነን። በሽምግልና/ ዕድሜ ክልል ያሉትን እሩጠዉ እንዲደርሱና ገስግሰዉ እንዲያጠቁልን መጠበቅ አንችልም። አሁን በታዳጊ ወጣትነት ደረጃ የሚገኙት ደግሞ የእኛን ፈለግ ከፋም ለማ መከተላቸዉ አይቀርም።ተዝለፍልፈን እንዳናዝለፍልፋቸዉ መጠንቀቅም ይገባናል ።ለዚህ ለማይቀረዉ ብሔራዊ ግዳጅ ወጣቶች በሕብረት እንነሣ!!

የኢትዮጵያ ወጣቶችን አኩሪ የጀግንነት ታሪክ ዛሬም ሕልዉ እናድርግ!!

ወጣቱ ትዉልድ ዛሬም የኢትዮጵያ ሕዝብ ተስፋ ነዉ!!!